

# የእሳት ልሳኖች

- አይሁዳውያን የተለያዩ በርካታ ሃይማኖታዊ በዓላትን እንዲያከብሩ በእግዚአብሔር ታዘዋል። ለምሳሌ ያህል የፋሲካን በዓል የሚያከብሩት የሞት መልአክ በመላ የግብፅ ምድር እየዞረ የግብፃውያንን በኩራት ሁሉ በሞት ሲቀጣ እስራኤላውያንን ግን 'ስላለፋቸውና' ከእነርሱ አንድም ሰው ስላልሞተ ነበር። የፋሲካን በዓል ካከበሩ ከአምሳ ቀን በኋላ ደግሞ የጴንጤ ቆስጤ ቀንን አከበሩ። ይህ የፋሲካ በዓል ከተከበረ ከኃምሳ ቀን በኋላ የሚያከብሩት በዓል በተጨማሪም በዓለ ኃምሳ  በመባል ይታወቃል። ይከበር የነበረውም የስንዴ ምርት ከተሰበሰበ በኋላ በዕለተ እሁድ  ለአንድ ሙሉ ቀን ነበር።

- በዚህ ታሪክ ውስጥ የተጠቀሱት ነገሮች የተፈፀሙት ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞተና ከሞት ከተነሳ በኋላ በተከበረው የጴንጤ ቆስጤ ቀን ላይ ነው። ብዙ በፀሎት የተጉ አይሁዳውያን የፋሲካን በዓል ለማክበር በኢየሩሳሌም ነበሩ። የመጡት ከተለያዩ አገሮች ስለነበር የተለያያ ቋንቋ ይናገሩ ነበር።

- በድንገት እነጴጥሮስ ተሰብስበው የነሩበትን ክፍል የኃይለኛ አውሎ ነፋስ  ድምፅ ሞላው።

- ከዚያም እሳት የሚመሳሰሉ ምላሶች ታዩ። በዚያ ተሰብስበው በነበሩት ላይም በእያንዳንዳቸው ላይ ተቀመጡባቸው። እያንዳንዳቸውም በተለየ ቋንቋ መናገር ጀመሩ።  መንፈስ ቅዱስ እነርሱ ራሳቸው በማይረዱት ቋንቋ ከሌሎች ጋራ እንዲግባቡ አደረጋቸው። ከአንድ የውጭ አገር ዜጋ ጋር ቋንቋውን ሳታውቁት በራሱ ቋንቋ ስትነጋገሩና ስትግባቡ መገመት ትችላላችሁ?

- እንደ አውሎ ነፋስ የመሰለው ድምፅ በጣም ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ በአካባቢው የነበሩ ሰዎች የሆነውን ነገር ለማየት ተሰበሰቡ። ከዚያም የሚደንቅ ነገር ሰሙ። እነኝህ ሰዎች የራሳቸውን ቋንቋ ሲናገሩ ይሰሟቸው ነበርና እጅግ በጣም ተደነቁ።  "ለመሆኑ እነኝህ ሰዎች ከገሊላ የመጡ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? ታዲያ እንዴት ነው እነኝህ ሰዎች የእኛን ቋንቋ ሊናገሩ የቻሉት?" አሉ።

❋ አንዳንዶች እነጴጥሮስ መጠጥ ጠጥተው የሰከሩ መሰሏቸው ነበር። ያ ግን ሊሆን የሚችል ነገር አልነበረም። ምክንያቱም ሰዓቱ ገና ከጥዋቱ 3፡00 ሰዓት ነውና! ብዙ የመጠጥ ሱስ ያለባቸው ሰዎች በዚያን ሰዓት መጠጥ አይጀምሩምና።

❋ ጴጥሮስም ከሌሎቹ አስራ አንድ ሐዋርያት ጋር ተነሳና የተሰበሰበውን ሕዝብ መስበክ ጀመረ። አሁን ስለሆነው ነገር ኢዩኤል የተባለው የብሉይ ኪዳን ነቢይ ትንቢት ተናግሮ እንደነበር በስብከቱ አስታወሳቸው። በመቀጠልም የናዝሬቱ ኢየሱስ  እንዴት እንደመጣ፣ እግዚአብሔርም የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት ለሰዎች ለማሳየት ምልክቶችንና ድንቆችን እንዴት በኢየሱስ አማካኝነት እንዳሳየ ሰበካቸው።

❋ ጴጥሮስ በተጨማሪም ኢየሱስን ለክፉ ሰዎች አሳልፈው መስጠታቸውን ጠቅሶ በዚያ የተሰበሰቡትን ሰዎች ከሰሳቸው። ጲላጦስ ኢየሱስን ሊፈታው ፈልጎ እያለ አይሁዳውያን ግን፣ "ስቀለው!" እያሉ እንደጮኹ እናስታውሳለን። ሮማውያን ኢየሱስን በመስቀል ላይ በሚስማር ጠርቀው መስቀላቸውንና መግደላቸውንም እናውቃለን።  እግዚአብሔርም ኢየሱስን ከሞት አስነሳው። ኢየሱስም ከሞት ከተነሳ በኋላ ለብዙዎች ታይቷል።

❋ በዚያ የተሰበሰበው ሕዝብ ከጴጥሮስ ስብከት በኋላ በኢየሱስ ላይ ያደረጉት ነገር ትክክለኛ ነገር አለመሆኑንና እንዲሁም በሕይወት ዘመናቸው የፈፀሙት ሁሉ ኃጢአት መሆኑን ሲረዱ  ተፀፀቱ። ስለዚህ "ወንድሞች ሆይ፣ ታዲያ ምን እናድርግ?" ብለው ጠየቋቸው።

❋ ጴጥሮስም እስከአሁን ድረስ ባደረጉት ኃጢአታቸው ተፀፅተው ንስሐ እንዲገቡ፣ የኃጢአታቸውን ይቅርታ እንዲቀበሉም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲጠመቁ ነገራቸው። ይህንን ካደረጉም እግዚአብሔር የሰጠውን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንደሚቀበሉና መንፈስ ቅዱስ ከእነርሱ ጋር እንደሚኖር ነገራቸው።

❋ የጴጥሮስን ስብከት ሰምተው የተቀበሉና በዚያን ቀን የተጠመቁ ሰዎች 3000 ያህሉ ነበር።

❋ ይህ ድንቅ ቀን ቤተ ክርስቲያን የተጀመረበችበት ቀን ነው።

*የጴንጤ ቆስጤ ታሪክ የሚገኘው በሐዋርያት ስራ ምዕራፍ 2፡ 1 – 40 ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com